

የትምህርት ዓመት 2026-2027

MCPS አጠቃላይ ዕቅድ

# ከባድ የአየር ሁኔታ በሚከሰት ጊዜ ቨርቹዋል ትምህርት የሚሰጥበት ዕቅድ



# ማውጫ


መግቢያ ....................................................................................3

የውሣኔ አሰጣጥ ..........................................................................4

ኮሙኒኬሽን................................................................................4

ትምህርት ላይ መገኘት እና የሚጠበቁ ነገሮች ..........................................6

የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራሞች ........................................................6

የጨቅላ ሕፃናት እና የትናንሽ ልጆችት ፕሮግራሞች ...................................6

የቅድመ ት/ቤት እና የሄድ ስታርት አጠቃላይ ትምህርት እና ልዩ ትምህርት .........7

ቻይልድ ፋይንድ/Child Find.......................................................7

እንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር ...............................................................8

የልዩ ትምህርት እና የተማሪ ድጋፍ አገልግሎቶች .......................................9

ቶማስ ኤዲሰን/የስራ ዝግጁነት ትምህርት አካዳሚ (CREA+)......................... 10

የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ፕሮግራሞች.......................................... 11

የጊዜ ሠሌዳዎች ......................................................................... 12

የውጤት አሰጣጥ......................................................................... 14

የተማሪዎች የትምህርት ምዘና/ግምገማ.............................................. 14

የኮምፕረሽንሲቭ ቴክኖሎጂ እቅድ .................................................. 14

የምግብ አቅርቦት ........................................................................ 16

# መግቢያ

በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ በተሰጠው መመሪያ እና በሜሪላንድ የትምህርት ኮድ፣ § 7-103.2 ድንጋጌ መሠረት፣ የአካባቢ ትምህርት ቤቶች በተወሰኑት ሕጋዊ መስፈርቶች መሠረት በመጥፎ የአየር ሁኔታ ወቅት ቨርቹዋል ትምህርት እንደሰጡ ተፈቅዶላቸዋል። እነዚህ መስፈርቶች ስለ አስተዳደር፣ ስለ ትምህርት፣ ስለ ተደራሽነት እና ስለ ተጠያቂነት የሚጠበቅባቸውን በግልጽ ያስቀምጣሉ። ቁልፍ የሆኑ ድንጋጌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ከቦርድ የተሰጠ ፈቃድ፡ የአካባቢው የትምህርት ቦርድ በከባድ የአየር ሁኔታ ወቅት ቨርቹዋል የትምህርት ቀናትን መጠቀም ሊፈቅድ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ በቦርዱ ስብሰባ ወቅት መከናወን አለበት፣ ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ለሱፐርኢንቴንደንቱ ቨርቹዋል ትምህርት የመተግበር ስልጣን እንዲሰጠው አዎንታዊ ድምጽ በመስጠት መደረግ አለበት።
- ለሕዝቡ ተደራሽ ማድረግ የጸደቀውን የቨርቹዋል ትምህርት ቀን እቅድ በትምህርት ስርዓቱ ድረ ገጽ ላይ በመለጠፍ ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለበት።
- በተመሳሳይ ጊዜ የሚሰጥ ትምህርት፦ ሱፐርኢንቴንደንቱ በከባድ የአየር ሁኔታ ምክንያት በቀን መቁጠሪያ ላይ ት/ቤቶች እንደሚዘጉ በእቅድ የተያዙት ሁሉም ቀኖች ጥቅም ላይ ውለው ከሆነ ብቻ በማጣራት ቨርቹዋል የማስተማር ቀን ተግባራዊ ማድረግ ይችላል። እያንዳንዱ ቨርቹዋል የትምህርት ቀን ቢያንስ አራት (4) ሰዓት የሚቆይ የተቀናጀ ትምህርት ማካተት አለበት።
- ትምሕርት ላይ መገኘት እና ተጠያቂነት የተማሪዎችም ሆነ የሰራተኞች በሥራ እና በትምህርት ላይ መገኘት መመዝገብ/ሪከርድ አለበት። ተማሪዎች በአካል ወደ ትምህርት ሲመለሱ ከቨርቹዋል የትምህርት ቀናት ጋር የተያያዙ ስራዎችን የማጠናቀቅ ወይም የማካካስ እድሎች ሊሰጣቸው ይገባል።
- ፍትሃዊ ተደራሽነት፡ የትምህርት ስርዓቱ ሁሉም ተማሪዎች በቨርቹዋል ትምህርት ለመሳተፍ አስፈላጊውን ቴክኖሎጂ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማገናኘት እንደሚችሉ ወይም አካዳሚክ ትምሕርት ሳያመልጣቸው አስፈላጊውን የትምህርት ስራ ለማጠናቀቅ አማራጭ መንገድ እንዳላቸው ማረጋገጥ አለበት።

ይህ እቅድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትምህርት ቤት ሕንፃዎች ለጥቂት ቀናት መክፈት በሚያዳግትበት ሁኔታ እንደሚቆዩ በሚገመት መጥፎ የአየር ሁኔታ ምክንያት ት/ቤቶች ሲዘጉ — ቢያንስ አራት (4) ሰዓት የሚፈጅ ስርዓተ ትምህርት — ወደ ቨርቹዋል ማስተማር መሸጋገር እንዲችሉ ይፈቅድላቸዋል።

ቨርቹዋል የትምህርት ቀናት በሜሪላንድ ሕግ መሠረት በሚያስፈልጉት 180 የትምህርት ቀናት ይቆጠራሉ እና በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት መመሪያ መሠረት በትምህርት ስርዓቱ ሁሉ ይተገበራሉ። የዚህ ዕቅድ ዓላማ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች፣ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ እና ቤተሰቦች የአሠራር ሁኔታዎች በአካል ት/ቤት መገኘት ካልተቻለ ወደ ቨርቹዋል ትምህርት መሸጋገር በሚያስፈልጋቸው ጊዜ የትምህርት ቀጣይነትን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉትን የአሠራር ለውጦች፣ ግብዓቶች፣ እና ድጋፎችን በቅድሚያ ተዘጋጅቶ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ለመግለፅ ነው።

ማሳሰቢያ፦ ሁሉም መጥፎ የአየር ሁኔታ የሚከስትባቸው ቀናት MCPS ወደ ቨርቹዋል የትምህርት ቀን ይሻገራል ማለት አይደለም። MCPS የኮሙኒኬሽን እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ዲቪዥን ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ እና ማህበረሰቡን ስለ ኦፕሬሽን ሁኔታ ለውጦችን ስለማሳወቅ የተቀመጡ ሂደቶችን እና እየተተገበረ ያለውን የከባድ አየር ሁኔታ ቀን በግልጽ ያሳውቃል።

ስለ ሜሪላንድ ቨርቹዋል የትምህርት ድንጋጌ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ቤተሰቦች እና ሰራተኞች MSDE የሰጠውን መመሪያ እዚህ እንዲመለከቱ እናበረታታለን።

# የውሳኔ አሰጣጥ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተማሪዎችና ሠራተኞች ደህንነትና ሠላም ዲስትሪክቱ ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። መጥፎ የአየር ሁኔታ ወይም ሌሎች የአደጋ ሁኔታዎች መደበኛ የትምህርት ቤት ስራዎችን ሲያስተጓጉሉ፣ MCPS ደህንነትን ቅድሚያ በመስጠት የትምህርት ቀጣይነትን ለመጠበቅ በርካታ አማራጮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ይገመግማል። እንደየሁኔታው፣ እነዚህ አማራጮች ት/ቤቶችን ዘግይቶ መክፈት ወይም ተማሪዎችን ቀደም ብሎ ከትምህርት ቤት ማሰናበት፣ ትምህርት ቤት ሙሉ ቀን እንዲዘጋ የመወሰን ወይም ቨርቹዋል ትምህርትን መተግበር የመሳሰሉ ውሳኔዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

የኦፕሬሽን ውሳኔዎች ሲደረጉ፣ MCPS የተለያዩ ነገሮችን ግምት ውስጥ ያስገባል፥ ከእነዚህም መካከል በብሔራዊ የአየር ትንበያ አገልግሎት የሚሰጡትን ወቅታዊ የአየር ትንበያዎች፣ የመንገድ እና የትራንስፖርት ደህንነት፣ የት/ቤት ህንፃዎች ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን፣ እና በአካል ትምህርት ለመስጠት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለመቀጠል ዝግጁ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሁኔታዎችን ያካትታሉ። መደበኛው በመጥፎ አየር ሁኔታ ወቅት ት/ቤቶችን የመዝጊያ ቀናት አሁንም እንደ አማራጭ ይቀጥላሉ። በሜሪላንድ ሕግ መሠረት፣ MCPS ቨርቹዋል የማስተማሪያ ቀንን ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በቀን መቁጠሪያ ላይ የተመደቡት የትምህርት ማካካሻ ቀናት በሙሉ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ ወደ ቨርቹዋል ትምህርት መሸጋገር ቻላል፦

- ቀደም ሲል በቀን መቁጠሪያ የተያዙት የትምህርት ማሚያ ቀናት በሙሉ ጥቅም ላይ የዋሉ ከሆነ
- በአስተማማኝ የአየር ሁኔታ ትንበያ ላይ ተመስርተው የክስተቱ ጊዜ እና ተጽእኖው ሊገመት የሚችል ከሆነ
- ዝግጅቱ ለብዙ ቀናት እንደሚቆይ የሚጠበቅ ከሆነ (ለምሳሌ፦ ጉልህ የሆነ ከባድ በረዶ እና አውሎ ነፋስ፣ እጅግ ቀዝቃዛ የበረዶ ክምችት ወይም ተመሳሳይ ድንገተኛ ሁነቶች)
- ከሠራተኞች፣ ከተማሪዎች፣ እና ከቤተሰቦች ጋር በቂ ቅድመ ዝግጅት እና ግንኙነት ተደርጎ ከሆነ

በመጥፎ የአየር ሁኔታ ወይም በሌሎች የደህንነት ስጋቶች ምክንያት ትምህርት ቤቶችን ለመዝጋት ወይም በስርዓት አቀፍ ደረጃ የሚደረግ ቨርቹዋል ትምህርት የሚሰጥበትን ቀን ተግባራዊ ለማድረግ የሚደረጉ ውሳኔዎች በዲስትሪክት ደረጃ የሚወሰኑ ሲሆን በሁሉም ትምህርት ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። MCPS በስርዓት አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ አቀራረብን መጠበቅ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትራንስፖርት አገልግሎቶች ላይ ጥገኛ በሆኑ የሕዝብ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ድርህንነት ከመጠበቅ አንጻር በአደጋ ጊዜ ምላሽ መስጠት ያስችለዋል።



# ግንኙነት

በመጥፎ የአየር ሁኔታ ጊዜ ወይም በአደጋ ጊዜ፣ ለመተማመን፣ የደህንነትን ሁኔታ ለማረጋገጥ፣ እና የትምህርት ቀጣይነትን ለመደገፍ ከሚመለከታቸው ጋር ግልጽ፣ ወቅታዊ፣ እና ወጥ የሆነ ግንኙነት አስፈላጊ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ ቤተሰቦችን እና ሰፊውን ማህበረሰብ የሚጠብቁ የመጥፎ አየር ሁኔታ ወይም ድንገተኛ አደጋ በትምህርት ቤት ስራዎች ላይ ለውጥ ማድረግ ሊያስፈልግ እንደሚችል፣ ይሄውም ወደ ቨርቹዋል የትምህርት ቀን መቀየርን ጨምሮ፣ ለተማሪዎች እና ለማህበረሰቡ ለማሳወቅ አስፈላጊ የሆኑ የግንኙነት ፕሮቶኮሎችን ያዘጋጃሉ።

MCPS የሚጠበቁ ነገሮችን እያከናወነ፣ በፍጥነት መፈፀም ያለባቸውን ነገሮች እየሠራ እና የተራዘመ የመጥፎ አየር ሁኔታ ትንበያ ወደፊት የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ከሚመለከታቸው ጋር በግልጽ የመረጃ ልውውጥ ማድረግን ቅድሚያ ይሰጣል። ሁኔታዎቹ በሚከሰቱበት ጊዜ ዲስትሪክቱ ቤተሰቦች ተገቢ የትምህርት መረጃ ሪሶርሶች እና ድጋፍ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ከማህበረሰብ አጋሮች እና ከመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ይሰራል። ግልጽ እና የተቀናጁ የግንኙነት እርምጃዎች የተዘረጉት ሁሉም ሰራተኞች ቨርቹዋል ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን እና ተማሪዎች ያለ ማቋረጥ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው።

# ዝግጅት እና በቅድሚያ ማሳወቅ

መጥፎ ወይም ከባድ የአየር ሁኔታ ወይም የአደጋ ሁኔታዎች ሲተነበዩ እና በቀን መቁጠሪያ ላይ የተመደቡት የትምህርት ማካካሻ ቀናት በሙሉ ጥቅም ላይ ውለው ከሆነ፣ MCPS በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ዝግጁነት እንዲኖር ለማድረግ በቅድሚያ ግንኙነት ያደርጋል።

» MCPS የኮሙኒኬሽን መምሪያ፣ ከትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር፣ ቨርቹዋል የትምህርት ቀን እንደሚኖር የሚጠበቅ ከሆነ "ተዘጋጁ/Get Ready" የሚል ማስታወቂያ ያወጣል። ይህ አስቀድሞ የሚደረግ ግንኙነት በማህበረሰቡ ውስጥ ዝግጁነት እንዲኖር እና የጋራ ኃላፊነትን መወጣት አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል።

  ይህ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት፡-

  - ትምህርት ቤቶችና መምህራን ትምህርት ለመስጠት መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣሉ እንዲሁም ለተማሪዎችና ለቤተሰቦች የሚጠበቅባቸውን ነገሮች ያሳውቃሉ።
  - አስተማሪዎች ተማሪዎችን ቨርቹዋል ለመማር ዝግጁ እንዲሆኑ እና ዲጂታል የመማር ተሞክሮ እና ተደራሽነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በቨርቹዋል የትምህርት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ።
  - ትምህርት ቤቶች ለቤት ውስጥ አገልግሎት የቴክኖሎጂ መገልገያዎችን ለሚጠይቁ ተማሪዎች መሳሪያዎችን እና ቻርጀሮችን ያከፋፍላሉ።

» የኮሙኒኬሽን መምሪያ በተቻለ ፍጥነት፣ የተቋቋሙ የመገናኛ ቻናሎችን በመጠቀም፣ ቨርቹወል የትምህርት ቀን ተግባራዊ የሚደረግበትን የመጨረሻውን ውሳኔ ያሳውቃል።

# የቤተሰብ ተሳትፎ እና ኃላፊነቶች

በቅድሚያ ማስታወቂያ በሚሰጥበት ጊዜ፣ ቤተሰቦች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡-

» የተማሪዎችን የጊዜ ሰሌዳዎች እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመመልከት ParentVue እና ParentSquare ተደራሽነት እንዳላቸው ማረጋገጥ አለባቸው።

» መረጃዎችን በፍጥነት ማግኘት እንዲችሉ የግንኙነት መረጃቸው ወቅታዊ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

» ተማሪዎች ለትምህርት እና ለኮርስ ስራ የሚያገለግሉ በዲስትሪክቱ የተፈቀደውን ዲጂታል የትምህርት መገልገያ መድረኮች/ፕላትፎርምስ ተደራሽነት እንዲኖራቸው መደገፍ

» MiFi መሳሪያዎች ትምህርት ማስተማርን ለመደገፍ በቤት ውስጥ የተዘረጉ ሲሆን (በመጥፎ የአየር ሁኔታ ወቅት ብቻ ሳይሆን) ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። አንድ ተማሪ MiFi የሚፈልግ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቶች መሳሪያው እንዲሰጥ እና ለአገልግሎት እንዲውል ፕሮግራም እንዲደረግ ጉግል ፎርም ላይ ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው። ተማሪያቸው አስተማማኝ የኢንተርኔት አገልግሎት ከሌላቸው ወይም በቨርቹዋል ትምህርት ለመሳተፍ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገው ከሆነ ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ አለባቸው።

  - የትምሕርት ቤት ሠራተኞች MiFi መገልገያ።ሉላችይ ቅየጠመ[ህዚእ]

# ስርዓት አቀፍ የመገናኛ ዘዴዎች

ቤተሰቦች እና ሰራተኞች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት የአሠራር ለውጦችን በተመለከተ መረጃ ያገኛሉ፥ ከእነዚህም ውስጥ፡

» MCPS [ድረ ገጽ]

  - MCPS በብዙ ቋንቋዎች የመረጃ ተደራሽነትን ለመደገፍ ድረ ገጹ በተለያዩ ቋንቋዎች የተተረጎሙ ጠቃሚ መረጃዎች አሉት።

» ኢሜል፣ የጽሑፍ መልዕክት፣ እና አውቶሜትድ የስልክ መልክቶች ይኖራሉ።

  - መልዕክቶች ParentSquare እና በኢሜል እንዲሁም በአካባቢው ትምህርት ቤት መደበኛ የመገናኛ ዘዴዎች ይተላለፋሉ።

» የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች

  - ፌስቡክ፣ X (ቀደም ሲል ትዊተር)፣ ኢንስታግራም፣ ሊንክደን እና ዩቲዩብ (Facebook, X (formerly Twitter), Instagram, LinkedIn, and YouTube)

» የአካባቢ ቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ጣቢያዎች

በሥራ ላይ ለውጦች በሚደረጉበት ጊዜ ስለ ት/ቤቶች ዘግይቶ መከፈት፣ ወይም ስለ ቨርቹዋል የትምህርት ቀናት፣ MCPS በመደበኛነት ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰጣል። እንደገና ት/ቤቶች የሚከፈቱበትን ጊዜ እና በአካል ወደ ትምህርትና ሥራ መመለስን የሚመለከት መረጃም አንድ ላይ መገለጽ ይኖርበታል።

# ደንብ ማክበር እና የሚጠበቁ ተግባራት



ቨርቹዋል ትምህርት በሚሰጥባቸው ቀናት፣MCPS ባቋቋመው የትምህርት ክትትል መቆጣጠሪያ ሂደት እና በዲስትሪክቱ የተማሪዎች የመረጃ ስርዓት፣Synergy በተመዘገበው መሰረት አስተማሪዎች እየተቆጣጠሩ ይመዘግባሉ። አስተማሪዎች ከጸደቀው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርዓተ ትምህርት ጋር የሚጣጣሙ የትምህርት ተግባሮችን ለተማሪዎች ይመድባሉ፣ ይሰበስባሉ፣ ይገመግማሉ እና ይመዘግባሉ። ተማሪዎች በመጥፎ የአየር ሁኔታ ምክንያት የሚሰጣቸውን ቨርቹዋል ትምህርት ሙሉ በሙሉ እንዲከታተሉ እና በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን የሚሰጡ ስራዎችን እንዲያጠናቅቁ ይጠበቅባቸዋል። ቨርቹዋል ትምህርት ማግኘት ያልቻሉ ተማሪዎች ውጤት ለማግኘት ያመለጣቸውን የትምህርት ስራዎች እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል።

ተማሪዎች Clever በመክፈት በዲስትሪክቱ የተፈቀዱ የትምህርት መድረኮችን (Canvas and Synergy StudentVUE) በመጠቀም ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የኮርስ ስራዎችን እና ሂደቱን በመከታተል ቨርቹዋል ትምህርት ያገኛሉ። ሪከርድ አስተማሪ በሲነርጂ ተሳትፎ ትምህርት ላይ መገኘትን እና የተጠናቀቁ ስራዎችን የመመዝገብ ኃላፊነት አለበት።

# የቀዳማይ ህጻናት ፕሮግራሞች

የወጣት ተማሪዎችን የእድገት ፍላጎቶች መገንዘብ፣ የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራሞች ቨርቹዋል የትምህርት መርሃ ግብሮች በፕሮግራም ሞዴል፣ በማስተማር ዲዛይን እና በአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርቶች ሊለያዩ ይችላሉ። የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራሞች የግማሽ ቀን እና የሙሉ ቀን አገልግሎቶችን ያካትታሉ፣ ይህም የቨርቹዋል ትምህርት አሰጣጥ እና እርምጃ ያሳውቃል።

ትምህርት ቤቶችና አስተማሪዎች የጊዜ ሰሌዳዎችን እና የሚጠበቁ ነገሮችን በቀጥታ ለቤተሰቦች ያስተላልፋሉ፣ ተማሪዎች ደግሞ ከፕሮግራሙ ግቦች ጋር በተጣጣሙ ባልተሰናሰነ (guided) የትምህርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

» ህፃናትና ትንንሽ ልጆች

» የቅድመ ት/ቤት ልዩ ትምህርት
Preschool Special Education

» ቅድመ መዋዕለ ህፃናት
Prekindergarten

» ሄድ ስታርት
Head Start

» ቻይልድ ፋይንድ
Child Find

# የህፃናትና ትንንሽ ልጆች ፕሮግራሞች

ለጨቅላ ሕፃናት እና ትናንሽ ልጆች፣ ለእያንዳንዱ ልጅ የግል የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) ወይም የተራዘመ IFSP (EIFSP) ላይ የተዘረዘሩት አገልግሎቶች በቨርቹዋል የትምህርት ወቅት ይቀጥላሉ። አገልግሎቶቹ የሚሰጡት በልጁ የዕለት ተዕለት ተግባራት እና ቤተሰብ ቨርቹዋል የወላጅ ክትትል በሚያደርግበት ክፍለ ጊዜ ነው። እነዚህ ክፍለጊዜዎች የእድገት እርምጃዎችን ለማበረታታት እና ቤተሰቦች የታለሙትን ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ የተነደፉ ናቸው። እያንዳንዱ ልጅ በፌዴራል እና በስቴት መስፈርቶች መሠረት IFSP ወይም EIFSP ላይ የተገለጹትን አገልግሎቶች እና የአገልግሎት ሰዓቶች ያገኛል።



# የቅድመ ት/ቤት እና ሄድ ስታርት አጠቃላይ ትምህርት እና ልዩ ትምህርት

የተናጠል ትምህርት ክፍለጊዜ ተማሪዎች የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን እንዲያገኙ እና የትምህርት ስራዎችን  እንዲያጠናቅቁ የሚያስችል ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን በራስ ፍጥነት፣ አስቀድሞ በተቀረጹ ትምህርቶች፣ የውይይት ሰሌዳዎች እና ዲጂታል የትምህርት መርጃዎች ይሰጣል፣ ይህም ብዙውን ጊዜ ለተለያዩ የጊዜ ሰሌዳዎች ተደራሽነትን እና ግላዊ ትምህርትን ይጨምራል። መጥፎ የአየር ሁኔታ ቀናት በሚኖሩበት ወቅት በአጠቃላይ ለቅድመ ት/ቤት ተማሪዎች ወይም የልዩ ትምህርት ይተገበራል። የልዩ ትምህርት ተማሪዎች እንቅስቃሴዎች ከእያንዳንዱ ተማሪ የግል ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ጋር የተጣመሩ ይሆናሉ።

የተናጠል ትምህርት ክፍለ ጊዜዎች፣ ተማሪዎች ለዕድሜያቸው ተመጣጣኝ የሆኑ፣ በአስተማሪዎች የሚመሩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እና የግላዊ ትምህርት እድገትን ለማበረታታት ከአዋቂዎች ድጋፍ ጋር ይተገበራሉ። እንቅስቃሴዎቹ ማህበራዊ መስተጋብርን የሚያበረታቱ እና ያለ ቴክኖሎጂ በቤት/የህፃናት እንክብካቤ ቦታዎች ላይ በአዋቂዎች ድጋፍ ሊተገበሩ የሚችሉ ለእድገት ተስማሚ የሆኑ ተግባራትን በተመለከተ ከተደረጉ ጥናቶች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው። የማስተማር መርሃ ግብሮቹ ቨርቹዋል የወላጅ ስልጠና ክፍለ ጊዜዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ በዚህ ጊዜ አስተማሪዎች የማስተማሪያ ስልቶችን ለመንደፍ እና የህጻናትን ትምህርት በቤት ውስጥ ለመደገፍ መመሪያ ለመስጠት ከቤተሰቦች ጋር በመተባበር ይሠራሉ።

# ቻይልድ ፋይንድ
# Child Find

"Child Find" ለማጣራት በክሊኒኮች እንደገና ቀጠሮ ይያዛል። የህፃናት የእድገት ግምገማ አገልግሎት (DESC) ቨርቹዋል ትምህርት በሚሰጥበት ወቅትም ይቀጥላል። መጥፎ የአየር ሁኔታ የሚከሰትባቸው ቀናት እንደሚኖሩ ቀደም ብሎ ሲታወቅ DESC እና ቻይልድ ፋይንድ ቡድኖች IEP ስብሰባ ቀኖችን እና ሰዓቶችን በተመለከተ ቤተሰቦችን ያነጋግራሉ። ተለይተው የሚታወቁ የመጥፎ አየር ሁኔታ ከባድ ቀናት ከመድረሳቸው በፊት፣DESC እና ቻይልድ ፋይንድ ቡድኖች ቨርቹዋል መድረኮችን ለማግኘት ወይም ግምገማዎችን ወይም IEP ስብሰባዎችን እንደገና ለማቀድ ከቤተሰቦች ጋር በመነጋገር ይሰራሉ። በይነ መረብ ላይ ትምህርት ለመማር የሚያገለግሉ ክሮምቡክስ/Chromebooks እና ሌሎች ዲጂታል መሳሪያዎች ለመጀመሪያ ግምገማ ወይም IEP ስብሰባ አይመደቡም።

# የእንግሊዝኛ ቋንቋን ማዳበር

በማንኛውም የሽግግር ጊዜ ቨርቹዋል ትምሕርት መሰጠት ይቀጥላል። ሁሉም ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ስለ ቨርቹዋል የትምህርት መዋቅሮች፣ ሂደቶች፣ እና የሚጠበቅባቸውን ማወቅ እና ማተኮር እንዲችሉ እንደአስፈላጊነቱ የተለያየ ቋንቋ ይጠቀሙ። በቅንጅት የሚሰጥ ትምህርት የሚቻል ከሆነ በጋራ ማስተማርን፣ በተናጠል መሥራትን እና በግላዊ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርትን ሊያካትት ይችላል። ከዚህ በታች ያሉት ምክረሃሳቦች ተማሪዎች የክፍል ደረጃ ትምህርት ይዘት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

| | ምርጥ ተሞክሮዎች እና ታሳቢ መደረግ ያለባቸው | ዕቅድ ማዘጋጀት |
|---|---|---|
| ስሜት እንዲሰጥ ማድረግ | » መረጃዎችን ግልጽ በሆኑ ምስሎች እና ወጥ በሆነ መንገድ ማደራጀት።<br>» የችግር አፈታት ሞዴል እና ከፍ አድርጎ ማሰብ።<br>» ግልጽ የሆኑ መስፈርቶችን በመጠቀም አፆ የግብረመልስ እድሎችን መስጠት።<br>» ተማሪዎች የሚቀርበውን ትምህርት ለመረዳት እንዲችሉ ተፈጥሯዊ ቋንቋቸውን እና የሥርዓተ ትምህርት አቀራረብን የቤት ቋንቋዎችን ጭምር በመጠቀም የትምህርት ግንዛቤን በጥልቀት ለመረዳት እና የትምህርት ውጤትን ለማሳደግ እንዲጠቀሙ መጋበዝ። | » ተማሪዎች በራሳቸው የይዘቱን ትርጉም መረዳት እንዲችሉ ለማድረግ እንዴት ያቅዳሉ?<br>» ተማሪዎች ትምህርቱን መከታተል የሚያስችላቸው ምን አይነት መሰላሎችን መስጠት/ማቅረብ ይችላሉ?<br>» ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ትርጉም ሰጥተው ለመረዳት እንዲችሉ ምን ዓይነት ስልቶችን መጠቀም ይቻላል?<br>» ለተማሪዎች የውይይት ጊዜ የተመደበላቸው የት ነው? |
| ችሎታን አሟጦ መጠቀም | » ውስብስብ በሆኑ ውይይቶች እና ተግባራት ላይ ለመሳተፍ ሰፊ እድል መስጠት።<br>» የተማሩትን መግለጽ እንዲችሉ በተለያየ ስልት እድሎችን መስጠት።<br>» ግልጽ የሆኑ መስፈርቶችን በመጠቀም አፆ ግብረመልስ እድሎችን መስጠት። | » ተማሪዎች የተማሩትን በተግባር ማሳየት እንዲችሉ እንዴት የተለያዩ እድሎችን መስጠት ይችላሉ?<br>» ለተማሪዎች ምን አይነት ትርጉም ያለው ድጋፍ መስጠት ይችላሉ? |
| ውይይቶችን ማዳበር | » የሞዴል ይዘት-ቋንቋ ተኮር።<br>» ትርጉም ያለው እና እውነተኛ መስተጋብር እንዲኖራቸው ለማድረግ የተለያዩ እድሎችን ይፍጠሩ።<br>» ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡ እና እንዲመልሱ እድል ይስጧቸው።<br>» ተማሪዎች በመረጡት ቋንቋ ስለ ትምህርት ይዘት እንዲወያዩ ጋብዟቸው።<br>» ለጠቅላላ ቡድን ከማቅረባቸው በፊት የሙከራ/የልምምድ ጊዜ ይስጧቸው (ንድፍ በማዘጋጀት ወይም በፈጣን ፅሁፎች፣ ወዘተ)። | » ተማሪዎች ሀሳባቸውን የሚገልጹት እንዴት ነው?<br>» ተማሪዎች በይዘቱ እና በተግባር ተሞክሮዎች መካከል እንዴት ግንኙነት ይፈጥራሉ?<br>» ለተቀናጀ ማስተማር፣ አነስተኛ የተማሪ ቡድኖችን ለማዘጋጀት ምን ማድረግ ይችላሉ? |
| የግንዛቤ ችሎታን መጠቀም = ንቃተ ህሊና ማለት የራስን ሀሳብ፣ ስሜት፣ እና የአእምሮ አስተሳሰብ በትክክል የመከተል ችሎታ ሲሆን ብዙውን ጊዜ የትኩረት አቅጣጫን በንቃተ ህሊና ማወቅን ያካትታል፣ በስሜት ብቻ ከመመራት ይልቅ፣ በተሻለ ሁኔታ ራስን መቆጣጠር፣ ስሜታዊ አስተሳሰብን መቀነስ እና ብልህነት ነው። | » ለማብራራት እና ግንኙነቶችን ለመፍጠር ሞዴል ቋንቋ ያስፈልጋል።<br>» የግንኙነት እና የማመዛዘን ሞዴል ማብራሪያ።<br>» የተወሰነ እና ቀጣይነት ያለው ግብረመልስ ይስጡ።<br>» በሙሉ የአካል ምላሽ እና እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም የአካዳሚክ ቋንቋ ድጋፍ ይስጡ። | » ተማሪዎችዎ ቋንቋን እነርሱ ካላቸው ዓላማ አንጻር ትርጉም ባለው ሁኔታ መጠቀም እንዲችሉ ምን አይነት እድሎችን መስጠት ይችላሉ?<br>» ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲያብራሩ ለመርዳት ምን አይነት የማስተማር እርምጃዎችን መጠቀም ይችላሉ?<br>» ተማሪዎች የጽሑፍ እና የንግግር ቋንቋቸውን እንዴት ማስፋፋት ይችላሉ? |

# ልዩ ትምህርት እና የተማሪ ድጋፍ አገልግሎቶች

## የአካል ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች

ከመዋእለ ህጻናት እስከ 21 ዓመት ዕድሜ ያሉ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በማንኛውም የቨርቹዋል ትምህርት ወቅት በተቻለ መጠን በግል የትምህርት ፕሮግራሞቻቸው (IEPs) የተለዩ ድጋፎችን እና አገልግሎቶችን ማግኘታቸው ይቀጥላል። ይህም በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ትምህርቶችን፣ ተዛማጅ አገልግሎቶችን (የንግግር ቋንቋ፣ ኦኩፔሽናል ቴራፒ፣ እና ፊዚካል ቴራፒ)፣ ማመቻቸት እና ተጨማሪ ድጋፎችን ያካትታል። ተማሪዎች ትምህርታቸው ቀጣይነት እና ተደራሽነት እንዲኖረው እና ወደ IEP ግቦቻቸው እንዲደርሱ ለማድረግ ተገቢ እና የሚቻል በሆነ መልኩ የሚሰጣቸውን አገልግሎት በቨርቹዋል ማቅረብ ያስፈልጋል።

## የትምህርት ቤት የሥነ ልቦና ባለሙያዎች/ሳይኮሎጅስቶች እና የሁለት ቋንቋ ግምገማ ቡድን አባላት

የትምህርት ቤት የሥነ ልቦና ባለሙያዎች እና የብዝሃ ቋንቋ ግምገማ ቡድን አባላት በቨርቹዋል ትምህርት ወቅት IEP እና ሰክሽን 504 ሂደቶችን ቀጣይነት ለመደገፍ ከትምህርት ቤት ቡድኖች ጋር ይተባበራሉ። አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ቨርቹዋል ስብሰባዎች ይካሄዳሉ። በርቀት ሊከናወኑ የሚችሉ የልዩ ትምህርት ግምገማዎች (ቃለመጠይቆች፣ የሪከርድ ግምገማዎች፣ እና የደረጃ መለኪያዎች) በቨርቹዋል ትምህርት ወቅት ሊከናወኑ ይችላሉ። ደረጃውን የጠበቀ የእውቀት (ኮግኒቲቭ) እና የአካዳሚክ ስኬት ፈተናን ጨምሮ በአካል መደረግ የሚያስፈልጋቸው የትምህርት ምዘና ግምገማዎች፣ በፈተና መስፈርቶች መሠረት በአካል የሚደረግ ግምገማ እስኪካሄድ ድረስ ለሌላ ጊዜ እንዲዘገዩ ይደረጋል። የትምህርት ምዘናና ግምገማ ሂደቱን ማካሄድ ከተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በቨርቹዋል ትምህርት ወቅት በክፍል ውስጥ ምዘናዎች ሊከናወኑ ይችላሉ።

## የካውንስሊንግ አገልግሎቶች

አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እና ሚስጥራዊነቱን መጠበቅ በሚቻልበት ጊዜ በግል ክፍለ ጊዜዎች ቨርቹዋል የምክር አገልግሎት/ካውንስሊንግ ሊሰጥ ይችላል። ግላዊነትን እና ሚስጥር መጠበቅ ስለሚያስፈልግ የቡድን ካውንስሊንግ ክፍለ ጊዜዎች በቨርቹዋል አይካሄዱም። ቨርቹዋል የምክር ክፍለ ጊዜ ከመካሄዱ በፊት፣ ሰራተኞች ሚስጥራዊነትን የመጠበቅ ሁኔታን ይገመግማሉ፣ እና በተቻለ መጠን በቤት ውስጥ የግል አመቺ ቦታ ለመለየት ከቤተሰቦች ጋር ማመቻቸት አለባቸው። ትምህርት ቤቶች የቨርቹዋል የምክር አገልግሎት አቅርቦትን እና የሚጠበቁ ነገሮችን የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ ለቤተሰቦች ያሳውቃሉ።

## የቴክኖሎጂ ድጋፍ እና ተደራሽነት

አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከዲስትሪክቱ የተፈቀደላቸው አጋዥ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂ በቨርቹዋል ትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ተማሪዎች በአካል ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት የሚጠቀሙባቸው አጋዥ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን እና የተደራሽነት ባህሪያትን ያገኛሉ።

## ልዩ ሙያ ያላቸው አገልግሎት ሰጪዎች

በቨርቹዋል ትምህርት ወቅት የድጋፍ እና የአገልግሎቶች አቅርቦትን ለማቀድ፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ልዩ ክፍለ ጊዜዎችን ወይም ሌሎች ቨርቹዋል ድጋፎችን መጠቀምን ጨምሮ ልዩ አገልግሎት ሰጪዎች ከክፍል አስተማሪዎች ጋር በመተባበር ይሠራሉ። ተማሪዎች በትምህርቱ ለመሳተፍ የሚያስፈልጋቸውን የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶች ወይም ግብዓቶች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ አቅራቢዎች ከቤተሰቦች ጋር በማስተባበር አስቀድመው ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። የመግለጫ ጽሑፍ ወይም ሌሎች አጋዥ ድጋፎችን የመሣሰሉ የተደራሽነት ባህሪያትን በማመቻቸት፣ ተማሪዎች ትምህርት እንዲያገኙ ለመርዳት ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

ለአስር (10) ቀናት ወይም ከዚያ በላይ የሚቆይ የተራዘመ የሚዘጋበት ጊዜ ሲኖር፣ ስለ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የትምህርት ምዘና ግምገማ ሂደቶች፣ እና መስፈርቶችን ስለመጠበቅ ለሠራተኞች እና ለቤተሰቦች ተጨማሪ መመሪያ ሊሰጥ ይችላል። IEP እና ሰክሽን 504 ስብሰባዎች በሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የስቴት እና የዲስትሪክት መመሪያዎች መሰረት በቨርቹዋል ማካሄድ ሊቀጥል ይችላል።

# ቶማስ ኢድሰን/የሙያ ትምህርት አካደሚ
# Thomas Edison/Career Readiness Education Academy (CREA+)

ቶማስ ኤዲሰን እና CREA+ ከባድ የአየር ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት ት/ቤት ዘግይተው የመክፈት የደወል መርሃ ግብር ጊዜ ይፈጥራሉ፣ PM (Edison & CREA) ክፍለ ጊዜንም ያካትታታል። የቶማስ ኤዲሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመጀመሪያ የአካባቢ ትምህርት ቤትን መርሃ ግብር መከተል አለባቸው። ከአካባቢያቸው ትምህርት ቤት መርሃ ግብር ጋር የሚጋጩ የኤዲሰን ትምህርቶች፣ በተናጠል ካንቫስ ላይ ትምህርቱ ይሰጣቸዋል።

# CREA+

## የግንኙነት መረብ

የትምህርት ስርዓቱ ማስታወቂያ ካወጣ በኋላ፣ በሠላሣ ደቂቃዎች ውስጥ የሚከተሉትን እናከናውናለን፡-

| ለሚመለከታቸው ሁሉ | ዘዴ | የመልእክቱ ይዘት |
|---|---|---|
| ሠራተኞች/አስተማሪዎች | አጭር የፅሑፍ መልእክት/ ኢሜል = SMS/Email | "የትምሕርት ስርዓቱ ሕንፃዎች ከተዘጉ 100% ወደ ቨርቹዋል እየተሸጋገርን ነው። ዙም ከፍቶ/ስብሰባ መግባት ያስፈልጋል" |
| ለተማሪዎች | Parent Square/ስልክ/ ኢሜል | በከባድ የአየር ሁኔታ ምክንያት “ዛሬ የማታ ትምህርት የሚሰጠው ቨርቹዋል/VIRTUAL (6-9pm) ነው። ሊንኩን ለማግኘት ኢሜልዎን ይመልከቱ" |

## የዲጂታል አገልግሎት ተደራሽነት

እያንዳንዱ ክፍል በመጨረሻ ደቂቃ ላይ የሚደረጉ የሊንክ መጋራትን ለማስቀረት በሴሚስተሩ መጀመሪያ ላይ "ቋሚ ቨርቹዋል አገናኝ" (ዙም) ሊኖረው ይገባል። በማንኛውም ቀን ፈረቃ ሊከሰት ስለሚችል፣ ሰራተኞች እና ተማሪዎች ለቨርቹዋል ክፍለጊዜ ዝግጁነት ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡-

- ቨርቹዋል ሊንክ/“Virtual Link”: እያንዳንዱ ክፍል የማይለወጥ ቋሚ ዙም/Zoom ሊንክ ሊኖረው ይገባል። ይሄን ማድረግ "አገናኙን ማግኘት አልቻልኩም" የሚለውን ችግር ይከላከላል።
- Mobile-First Design: ብዙ ተማሪዎች ቤታቸው ውስጥ ላፕቶፕ ከሌላቸው በስልኮቻቸው ይገባሉ። ሁሉም PDFs እና ስላይዶች በትንሽ ስክሪን ላይ ሊነበቡ የሚችሉ መሆናቸውን አረጋግጡ።
- የኢንተርኔት ግንኙነት ከሌለው/ከተቋረጠበት አንድ ተማሪ የኤሌክትሪክ/Wi-Fi አገልግሎት ከተቋረጠበት/ከሌለው፣ አስቀድሞ የተመደበለት “የከባድ አየር ሁኔታ ፓኬት” (በሕትመት ወይም በድረገጽ ላይ) ትምህርት ላይ ስለመገኘቱ(ቷ) ክሬዲት ሊኖረው/ሊኖራት ይገባል።

| ይዘት | ኃላፊነት | ተግባር |
|---|---|---|
| የስብሰባ አገናኝ/Meeting Links | አስተማሪዎች | በዓመቱ መጀመሪያ ካንቫስ ክፍል ላይ ተደጋጋሚ አገናኝ/links ይለጥፉ። ትምህርት ቤት በሚጀመርበት ሳምንት ውስጥ የመክፈት/logging ልምምድ ያድርጉ እና ከዚያ በኋላ ከአዲሱ የተማሪዎች መግለጫ ጋር ያገናኙት። |
| የቴክኖሎጂ ድጋፍ | የፕሮግራም ቴክኖሎጂ መሪ | አስተባባሪው፣ ETC፣ የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ እና የቅበላ ባለሙያው(ዋ) ተማሪዎችን በቴክኒክ ጉዳዮች ለመርዳት ሌሊቱን ሙሉ "ክፍት በሆነ የእገዛ ዴስክ/Live Help Desk" ሊንክ ይቆጣጠራሉ። |
| ትምህርት መከታተል | አስተማሪዎች | በቦታው መኖራቸውን/መገኘታቸውን ለመቆጣጠር ሲነርጂ/synergy ይጠቀሙ |



## የተቀናጀ/Synchronous መርኃግብር (6:00 PM – 9:00 PM)

"የዙም መሠላቸትን" ለመከላከል 50/10/50 ከፋፍለን እንጠቀማለን።

- 6:00 PM – 6:15 PM: ዲጂታል "ሶፍት ስታርት" (ቼክ-ኢንስ፣ የቴክኖሎጂ ችግር ካጋጠመ ለመርዳት እና ዓላማ)
- 6:15 PM – 7:15 PM: በቀጥታ ማስተማር / ጠቅላላ የቡድን ውይይት።
- 7:15 PM – 7:30 PM: ስክሪን ይዘጋል (ተማሪዎች የሚጠቀሙበትን የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች እንዲያቋርጡ ያበረታቷቸው)።
- 7:30 PM – 8:30 PM: በቡድን ተከፋፍለው የሚሠሩበት ክፍለጊዜ /በአነስተኛ ቡድን በትብብር ይሠራሉ።
- 8:30 PM – 9:00 PM: ሀሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት፣ ጥያቄና መልስ/Q&A እና ማጠቃለያ

## ዕለታዊ ክትትል

በሚቀጥለው ጥዋት የአስተዳደር ቡድኑ ማንኛውም ተማሪ በትምህርት መርጃ ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ መገናኘት ካልቻለ(ች) በትምህርቱ ላይ ለመሳተፍ የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ቴክኖሎጂ እንዳለው/እንዳላት ለማረጋገጥ ያነጋግራል።

# የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ፕሮግራሞች

ሁሉም የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ፕሮግራሞች (CTE) የሚካሄዱት ቨርቹዋል ነው። ከትምህርት ቦታ ውጭ ለሚደረጉ የሥራ ተለማማጅነት እና ሌሎች ተግባሮች የሚከናወኑት በቨርቹዋል ሲሆን ከኢንተርንሽፕ ኮኦርዲኔተር ወይም (ከተቻለ) ከሥራ ቦታው በሚሰጥ ድጋፍ ቨርቹዋል በመሳተፍ ነው። መቀጠል ያለባቸው የሚከፈልባቸው ስራዎችን በተመለከተ፣ ተማሪዎች እና/ወይም የአካባቢ ትምህርት ቤት አስተባባሪዎች በአየር ሁኔታ ምክንያት ተገቢ የሆኑ ደህንነታቸው የተጠበቀ ዝግጅቶችን ለማድረግ ከአሠሪው እና ከወላጆች ጋር በቀጥታ መስራት አለባቸው።

# የጊዜ ሠሌዳ



ትምህርት ቤቶች 2 ሰዓት የዘገየ የቨርቹዋል ትምህርት መርሃ ግብር ይከተላሉ።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች በመደበኛ የስራ ሰዓታቸው መሰረት ይሰራሉ።

- ሁለት ሰዓት ዘግይቶ የመጀመር ዓላማው መምህራን እና ሁሉም ሰራተኞች ለቨርቹዋል የትምሕርት ቀን በቂ ጊዜ ኖሯቸው እንዲዘጋጁ ለማስቻል ነው
- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (HS)፣ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (MS) እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ES) 9:45 am፣ 10:15 am፣ እና 11:00/11:25 am በአግባቡ ማስተማር ለመጀመር መዘጋጀት አለባቸው።
- የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሠመር የትምህርት አመራር ቡድን ስብሰባቸው ወቅት በጊዜ ሰሌዳው ላይ ከተዘረዘረው የጊዜ ገደብ ጋር ተስማሚ የሆነ የትምህርት ይዘቶችን ይወስናሉ።
- ትምህርት ቤቶች ስለ መርሃ ግብሮች እና ስለ ዙም/Zoom አገናኝ የትምህርት ቤቶቻቸውን ልዩ መረጃዎች ከዋናው ዶኩመንት ጋር ከኦክቶበር 8, 2026 በፊት ተማሪዎች የሚያገናኙትን ፈጣን ተደራሽ የሆነ የቨርቹዋል ትምሕርት ዕቅዳቸውን ማገናኘት አለባቸው። ትምህርት ቤቶች ኦክቶበር 15, 2026 እና ኖቨምበር 18, 2026 ላይ ኮምፒውተሮችን ማገናኘት፣ ካንቫስ መክፈትና ማገናኘት፣ እና ዙም/Zoom መክፈትና ማገናኘት የመሣሰሉትን ሁለት ዙር ልምምዶችን ያካሂዳሉ። ይህ ዋና ዶኩመንት ለቨርቹዋል ማስተማር በተዘጋጀው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድረ ገጽ ጋር ይገናኛል።

ትምህርት ቤቶች/መምህራን በቨርቹዋል የትምህርት ቀን ጠዋት ላይ ስለ ክፍላቸው/ክፍሎቻቸው ተገቢውን መረጃ የያዘ ኢሜይል ይልካሉ። አንድ ቋንቋ ለናሙና ከዚህ በታች ተያይዟል

ናሙና የኢሜይል ቴምፕሌት

**የጊዜ ሰሌዳው እንደሚከተለው ነው:-**

## ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቨርቹዋል ትምህርት መርሃ ግብር

| ክፍለጊዜ | የሚጀመርበት ሠዓት | የሚጠናቀቅበት ሰአት | የሚቆይበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ክፍለጊዜ - | 9:45 AM | 10:17AM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 10:17 AM | 10:20 AM | 3 ደቂቃ |
| 2ኛ ክፍለጊዜ | 10:20 AM | 10:52 AM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 10:52 AM | 10:55 AM | 3 ደቂቃ |
| 3ኛ ክፍለጊዜ | 10:55 AM | 11:27 AM | 32 ደቂቃ |
| የምሳ ሠዓት | 11:27 AM | 11:57 AM | 30 ደቂቃ |
| 4ኛ ክፍለጊዜ | 11:57 AM | 12:29 PM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 12:29 PM | 12:32 PM | 3 ደቂቃ |
| 5ኛ ክፍለጊዜ | 12:32 PM | 1:04 PM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 1:04 PM | 1:07 PM | 3 ደቂቃ |
| 6ኛ ክፍለጊዜ | 1:07 PM | 1:39 PM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 1:39 PM | 1:42 PM | 3 ደቂቃ |
| 7ኛ ክፍለጊዜ | 1:42 PM | 2:13 PM | 32 ደቂቃ |

## ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

### BLOCK የጊዜ ሰሌዳ ለሚከተሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቨርቹዋል ማስተማር መርሃ ግብር

| ክፍለጊዜ | የሚጀመርበት ሠዓት | የሚጠናቀቅበት ሰአት | የሚቆይበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| አንደኛ ብሎክ Block 1 | 9:45 AM | 10:43 AM | 58 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 10:43 AM | 10:46 AM | 3 ደቂቃ |
| ሁለተኛ ብሎክ Block 2 | 10:46 AM | 11:44 AM | 58 ደቂቃ |
| የምሳ ሠዓት | 11:44 AM | 12:14 PM | 30 ደቂቃ |
| ሦስተኛ ብሎክ Block 3 | 12:14 PM | 1:12 PM | 58 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 1:12 PM | 1:15 PM | 3 ደቂቃ |
| አራተኛ ብሎክ Block 4 | 1:15 PM | 2:13 PM | 58 ደቂቃ |

# መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
# የቨርቹዋል ትምህርት መርሃ ግብር

| ክፍለጊዜ | የሚጀመርበት ሠዓት | የሚጠናቀቅበት ሰአት | የሚቆይበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ክፍለጊዜ | 10:15 AM | 10:47 AM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 10:47 AM | 10:50 AM | 3 ደቂቃ |
| 2ኛ ክፍለጊዜ | 10:50 AM | 11:22 AM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 11:22 AM | 11:25 AM | 3 ደቂቃ |
| 3ኛ ክፍለጊዜ | 11:25 AM | 11:57 AM | 32 ደቂቃ |
| የምሳ ሠዓት | 11:57 AM | 12:27 PM | 30 ደቂቃ |
| 4ኛ ክፍለጊዜ | 12:27 PM | 12:59 PM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 12:59 PM | 1:02 PM | 3 ደቂቃ |
| 5ኛ ክፍለጊዜ | 1:02 PM | 1:34 PM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 1:34 PM | 1:37 PM | 3 ደቂቃ |
| 6ኛ ክፍለጊዜ | 1:37 PM | 2:09 PM | 32 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 2:09 PM | 2:12 PM | 3 ደቂቃ |
| 7ኛ ክፍለጊዜ | 2:12 PM | 2:44 PM | 32 ደቂቃ |

## መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

### ቨርቹዋል ትምሕርት የሰጥበት የጊዜ ሠሌዳ - 8 ክፍለጊዜዎች

| ክፍለጊዜ | የሚጀመርበት ሠዓት | የሚጠናቀቅበት ሰአት | የሚቆይበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ ክፍለጊዜ | 10:15 AM | 10:44 AM | 29 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 10:44 AM | 10:47 AM | 3 ደቂቃ |
| 2ኛ ክፍለጊዜ | 10:47 AM | 11:16 AM | 29 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 11:16 AM | 11:19 AM | 3 ደቂቃ |
| 3ኛ ክፍለጊዜ | 11:19 AM | 11:48 AM | 29 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 11:48 AM | 11:51 AM | 3 ደቂቃ |
| 4ኛ ክፍለጊዜ | 11:51 AM | 12:21 PM | 30 ደቂቃ |
| የምሳ ሠዓት | 12:21 PM | 12:51 PM | 30 ደቂቃ |
| 5ኛ ክፍለጊዜ | 12:51 PM | 1:20 PM | 29 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 1:20 PM | 1:23 PM | 3 ደቂቃ |
| 6ኛ ክፍለጊዜ | 1:23 PM | 1:52 PM | 29 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 1:52 PM | 1:55 PM | 3 ደቂቃ |
| 7ኛ ክፍለጊዜ | 1:55 PM | 2:24 PM | 29 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 2:24 PM | 2:27 PM | 3 ደቂቃ |
| 8ኛ ክፍለጊዜ | 2:27 PM | 2:57 PM | 30 ደቂቃ |

## Tier 1 የሚጀመርበት ሠዓት

**አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ቨርቹዋል ትምህርት የሚሰጥበት የጊዜ ሠሌዳ**

ልዩ ትምህርት በማይሰጥባቸው ቀናት ብሎክስ/Blocks ይጣመራሉ።

| ክፍለጊዜ | የሚጀመርበት ሠዓት | የሚጠናቀቅበት ሰአት | የሚቆይበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| ዙም ክፈቱ/Log in on Zoom | 10:45 AM | 11:00 AM | 15 ደቂቃ |
| 1ኛ ክፍለጊዜ | 11:00 AM | 11:45 AM | 45 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 11:45 AM | 11:49 AM | 4 ደቂቃ |
| 2ኛ ክፍለጊዜ | 11:49 AM | 12:34 PM | 45 ደቂቃ |
| የምሳ ሠዓት | 12:34 PM | 1:19 PM | 45 ደቂቃ |
| 3ኛ ክፍለጊዜ | 1:19 PM | 2:04 PM | 45 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 2:04 PM | 2:08 PM | 4 ደቂቃ |
| 4ኛ ክፍለጊዜ | 2:08 PM | 2:38 PM | 30 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 2:38 PM | 2:42 PM | 4 ደቂቃ |
| 5ኛ ክፍለጊዜ | 2:42 PM | 3:12 PM | 30 ደቂቃ |

በየክፍለጊዜዎቹ የሚቀርቡት ትምህርቶች ELA፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ/ማህበራዊ ጥናት (ሶሻል ስተዲስ) እና ልዩ ትምህርቶችን ማካተት አለባቸው። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ክፍለጊዜ በመርሃግብሩ ውስጥ ሊካተት ይችላል።

## Tier 2 የሚጀመርበት ሠዓት

**አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ቨርቹዋል ትምህርት የሚሰጥበት የጊዜ ሠሌዳ**

ልዩ ትምህርት በማይሰጥባቸው ቀናት ብሎክስ/Blocks ይጣመራሉ።

| ክፍለጊዜ | የሚጀመርበት ሠዓት | የሚጠናቀቅበት ሰአት | የሚቆይበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| ዙም ክፈቱ/Log in on Zoom | 11:10 AM | 11:25 AM | 15 ደቂቃ |
| 1ኛ ክፍለጊዜ | 11:25 AM | 12:10 PM | 45 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 12:10 PM | 12:14 PM | 4 ደቂቃ |
| 2ኛ ክፍለጊዜ | 12:14 PM | 12:59 PM | 45 ደቂቃ |
| የምሳ ሠዓት | 12:59 PM | 1:44 PM | 45 ደቂቃ |
| 3ኛ ክፍለጊዜ | 1:44 PM | 2:29 PM | 45 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 2:29 PM | 2:33 PM | 4 ደቂቃ |
| 4ኛ ክፍለጊዜ | 2:33 PM | 3:03 PM | 30 ደቂቃ |
| የሽግግር ሰዓት | 3:03 PM | 3:07 PM | 4 ደቂቃ |
| 5ኛ ክፍለጊዜ | 3:07 PM | 3:37 PM | 30 ደቂቃ |

በየክፍለጊዜዎቹ የሚቀርቡት ትምህርቶች ELA፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ/ማህበራዊ ጥናት (ሶሻል ስተዲስ) እና ልዩ ትምህርቶችን ማካተት አለባቸው። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ክፍለጊዜ በመርሃግብሩ ውስጥ ሊካተት ይችላል።

**ማሳሰቢያ፡-**

ቶማስ ኤዲሰንከባድ የአየር ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት የራሳቸውን የጧት እና የከሰዓት በኋላ ክፍለ ጊዜዎች የጊዜ ሰሌዳ ደወል ይፈጥራሉ። የቶማስ ኤዲሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመጀመሪያ የአካባቢ ትምህርት ቤትን መርሃ ግብር መከተል አለባቸው። ከአካባቢያቸው ትምህርት ቤት መርሃ ግብር ጋር የሚጋጩ የኤዲሰን ትምህርቶች፣ በተናጠል ካንቫስ ላይ ትምህርቱ ይሰጣቸዋል።

ሁሉም የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ፕሮግራሞች (CTE) ቨርቹዋል ማስተማር ይቀጥላሉ። ከትምህርት ቦታ ውጭ ለሚደረጉ የሥራ ተለማማጅነት እና ሌሎች ተግባሮች የሚከናወኑት በቨርቹዋል ሲሆን ከኢንተርንሽፕ ኮኦርዲኔተር ወይም (ከተቻለ) ከሥራ ቦታው በሚሰጥ ድጋፍ ቨርቹዋል በመሳተፍ ነው። መቀጠል ያለባቸው የሚከፈልባቸው ስራዎችን በተመለከተ፣ ተማሪዎች እና/ወይም የአካባቢ ትምህርት ቤት አስተባባሪዎች በአየር ሁኔታ ላይ በመመስረት ተገቢ የሆኑ ደህንነታቸው የተጠበቀ ዝግጅቶችን ለማድረግ ከአሠሪው እና ከወላጆች ጋር መስራት አለባቸው።

የጨቅላ ሕፃናት እና የትናንሽ ልጆች ፕሮግራም አገልግሎቶች አሁን ባለው 2 ሰዓት የዘገየ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከጠዋቱ 10፡00 AM. ጀምሮ ይሰጣሉ። ከጠዋቱ 10፡00 AM በፊት ለማካሄድ የታቀዱ ግምገማዎች እና IFSP እድገት በሌላ ጊዜ ጠዋት 10፡00 AM ወይም በጋራ በተስማሙበት ሰዓት እንደገና ይካሄዳሉ።

# ስለ ማርክ አሠጣጥ

የተማሪዎች የትምህርት ውጤቶች ቨርቹዋል ትምህርት በተሰጠበት ተመሳሳይ ወቅት ሊሰበሰቡ ይችላሉ፣ ነገር ግን የትምሕርት ክፍሎች፣ PLC ወይም የኮርስ ቡድኖች ከትምህርት ቤቱ የአመራር ቡድን ጋር በመተባበር በቨርቹዋል ትምህርት ወቅት የትምህርት ሥራዎችን በመስጠት እና ፍትሃዊ የውጤት አሰጣጥ ተግባሮችን ወጥነት ለመፍጠር በመተባበር መቀጠል አስፈላጊ ነው። በተቀናበረ ትምህርት ወቅት የቤት ስራዎች ስለሚሰጡ፣ ተማሪዎች በትምህርት ላይ እንዲገኙ ይበረታታሉ።

MSDE መስፈርቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ ሁሉም ተማሪዎች በመጥፎ የአየር ሁኔታ ቀናት ውስጥ ያመለጣቸውን የተቀናጀ ቨርቹዋል የትምሕርት ስራ የማካካስ እድል ይኖራቸዋል።

# የተማሪ የትምህርት ምዘናዎች/ ግምገማዎች



ቨርቹዋል ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት የስቴት የትምህርት ግምገማዎች አይካሄዱም።

- በስቴት የፈተና መስጫ ወቅት ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ማስተካከያዎች MSDE ከተገለጹ መቼ እንደሚደረጉ ለትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ/STC ይገለጻሉ።
- ቨርቹዋል ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት የዲስትሪክት የትምህርት ምዘናዎች/ ግምገማዎች መካሄድ የለባቸውም።
- መምህራን ከቡድኖች፣ ከዲፓርትመንቶች፣ እና PLCs ጋር በመተባበር የክፍል ፈተና/ግምገማ መስጠት ካለባቸው በጥንቃቄ ይወስናሉ።

# አጠቃላይ/ኮምፕርሽንሲቭ የቴክኖሎጂ ዕቅድ

MCPS ቨርቹዋል ትምህርት በሚሰጥባቸው ቀናት በሙሉ አስፈላጊው ሲስተም ተደራሽ መሆኑን፣ አስተማማኝ መሆኑን፣ አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መዘጋጀታቸውን እና የማስተማሪያ ቴክኖሎጂ ድጋፍ መኖሩን ያረጋግጣል። ዲስትሪክቱ ቤተሰቦች እና ትምህርት ቤቶች አስቀድመው ለመዘጋጀት ምን ማድረግ እንዳለባቸው፤ እና ስኬታማ የሆነ የአንድ ቀን ወይም ለበርካታ ቀናት ቨርቹዋል ትምህርት ለመስጠት ምን እንደሚያስፈልግ የሚያብራራ ሁሉን አቀፍ የቴክኖሎጂ እቅድ አዘጋጅቷል።

እያንዳንዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ከትምህርት ቤት የሚሰጡትን ቨርቹዋል የተቀናጀ ትምህርት ላይ ለመሳተፍ፣ የቤት ስራዎችን ለማጠናቀቅ እና ከትምህርት ቤት የተሰጠ ስራ ጨርሶ ለማስረከብ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እና የበይነመረብ ተደራሽነት ይኖረዋል/ ይኖራታል። ቤተሰቦች መጥፎ የአየር ሁኔታ ቀን ከመጀመሩ በፊት ከመምህራን የሚላኩ መልዕክቶችን ለማግኘት ParentSquare እና myMCPS Classroom ወይም Canvas inbox መመልከት አለባቸው።

## የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (ዲቫይስስ)

እያንዳንዱ የትምህርት መርጃ መሳሪያ የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ፣ ቨርቹዋል ትምሕርት በሚሰጥበት ወቅት የሚጠቀምበት/የምትጠቀምበት ክሮምቡክ/Chromebook እና ቻርጀር ይሰጠዋል። ተማሪዎች የተሰጣቸውን የትምህርት መሳሪያ እና ቻርጀር ወደ ቤታቸው የሚወስዱበት ቦርሳ ይዘው መምጣት አለባቸው። የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች MiFi ዲቫይስ መጠየቅ ይችላሉ፣ ትምህርት ቤቶችም የሚያስፈልገውን የመጠየቂያ ቅጽ ይሞላሉ/ያስሞላሉ።

እያንዳንዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተማሪ ቨርቹዋል ትምህርት ለመስጠት የሚያስፈልገውን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ከዲስትሪክቱ ማግኘት ይችላል። አስተማሪዎች ሁሉም የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በትክክል መዘጋጀታቸውን እና መስራታቸውን ለማረጋገጥ ካሜራዎች፣ ማይክሮፎኖች እና ድጋፍ ሰጪ ሪሶርሶች ይኖራቸዋል።

# መተግበሪያ ግብዓቶች/ሪሶርሶች እና ድጋፍ

MCPS ቨርቹዋል ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት ተማሪዎችን ለመርዳት የተለያዩ ግብዓቶችን/ሪሶርሶችን እና መመሪያዎችን ይሰጣል። እነዚህ ግብዓቶች myMCPS Classroom (Canvas) እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው አጋዥ ስልጠናዎችን፣ ዙም (Zoom) ስብሰባዎችን መቀላቀል የሚችሉበት መመሪያ፣ አጠቃላይ የዙም (Zoom) ተጠቃሚ መመሪያ እና ክሮምቡክስ (Chromebooks) ድንገት ካልሠራ የሚያስተካክሉበት ድጋፍ የሚያገኙበት/መመሪያ ያካትታሉ። ተጨማሪ እገዛ ለመስጠት የማህበረሰብ የቴክኖሎጂ ድጋፍ ፖርታል ይኖራል። ቤተሰቦች እና ተማሪዎች የሚከተሉትን የትምህርት መርጃ ሪሶርሶች/መገልገያዎች ማግኘት ይችላሉ፡

» MCPS Passport to Canvas - ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች

» MCPS Passport to Canvas - ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች

» ተማሪዎች አገልግሎት የሚያገኙበት ዙም (Zoom for Students)

» አጠቃላይ የዙም (Zoom) ተጠቃሚ መመሪያ

» ክሮምቡክ (Chromebook) የሆነ ችግር ቢፈጠር ችግሩን ለመፍታት የሚረዳ መመሪያ/Chromebook Troubleshooting Guide

» የማህበረሰብ ቴክ ድጋፍ ፖርታል

አስተማሪዎች መጥፎ የአየር ሁኔታ ከመከሰቱ በፊት በቨርቹዋል የትምህርት ቀን ስለሚጠበቅባቸው ነገሮች ለተማሪዎች መመሪያ  ይሰጣሉ። ይህም myMCPS Classroom ወይም Canvas እንዴት እንደሚከፍቱ፣ የኮርስ ዝርዝሮችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ እና Google Docs፣ Slides እና Drive የመሳሰሉ ለቨርቹዋል ትምህርት የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ አፕሊኬሽኖችን ያካትታል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተማሪዎች ለቨርቹዋል ትምህርት የሚዘጋጁበት ድጋፍ እና መመሪያም ያገኛሉ። ያሉት ድጋፎች የግንኙነት ቴምፕሌቶች፣ቨርቹዋል ማስተማሪያ ግብዓቶች/ሪሶርሶች እና የእገዛ ዴስክ ፖርታል ናቸው። ትምህርት ቤቶች በሙሉ በየግላቸው ድጋፍ ማግኘት እንዲችሉ የተለየ የቴክኖሎጂ ስፔሻሊስት (TIS) ተመድቦላቸዋል። የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች የመደቧቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች ከተመደበላቸው (TIS) እርዳታ ማግኘት በሚያስፈልጋቸው ጊዜ አስፈላጊውን የአፈጻጸም ሂደት ይወስናሉ። አስተማሪዎች ቨርቹዋል ለማስተማር ተደጋጋሚ የዙም ስብሰባዎችን ስለማዘጋጀት መመሪያ ይሰጣቸዋል።

# የተጠቃሚ ኃላፊነቶች

ተማሪዎች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የቀረበ ቴክኖሎጂን MCPS ደንብ IGT-RA ድንጋጌ መሰረት፣ ስለ ኮምፒውተር ሲስተሞች  የተጠቃሚ ኃላፊነቶች፣ ስለ ኤሌክትሮኒክስ መረጃ፣ እና ስለ ኔትወርክ ደህንነት እንደተገለፀው ለትምህርት ዓላማዎች ብቻ እንዲጠቀሙ ይጠበቅባቸዋል። የኮምፒውተር መሳሪያዎች፣ ዲጂታል አገልግሎቶች እና የኔትወርክ ተደራሽነት በሙሉ የሚሰጡት ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለማስተማር እና ተልዕኮ ለመደገፍ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎችና ኔትወርኮች አጠቃቀም ሊገመገም እና ሊመዘገብ ይችላል።

ተማሪዎች ከስርቆት፣ ከብልሽት፣ ያልተፈቀደ ተደራሽነት፣ ከጣልቃ ገብነት እና እንዳይጠፋ በመከላከል መረጃዎችን እና ሪሶርሶችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ቴክኖሎጂ ሲጠቀሙ ሁሉንም ተዛማጅ የስቴት፣ የአካባቢ፣ እና የፌዴራል ህጎችን የማክበር ኃላፊነት አለባቸው።

መመሪያዎቹን በሙሉ እዚህ ማግኘት ይቻላል፡-  IGT-RA

# የምግብ አቅርቦት

ያልተጠበቀ የትምህርት ቤቶች መዘጋት የቨርቹዋል ማስተማር ጭምር በሚከሰትበት ወቅት፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኦፕሬሽን ቡድን ትምህርት ቤቶችን እንደገና ስለመክፈት ቅድሚያ ይሰጣል፣ ለሁሉም ተማሪዎች የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት ይሰጣል። በተጨማሪም፣ DFNS ለድንገተኛ ተጨማሪ የምግብ ስርጭት አስፈላጊነቱን እንደሚከተለው ይገመግማል፦

1. ክፍያን መሠረዝ

   ባልተጠበቀ ሁኔታ ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ጊዜ ምግብ ለማቅረብ ከ MSDE ፈቃድ ያስፈልጋል።

2. የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ አገልግሎት - ቀን 3

   - ደህንነት፣ ተደራሽነት፣ አቅርቦት፣ የሰው ኃይል እና የመገልገያ አገልግሎቶች ላይ በመመስረት፣ በካውንቲው ውስጥ የሚገኙ አስቀድሞ ከተለዩት የምግብ ማከፋፈያ ጣቢያዎች የተወሰኑ ቦታዎች ለምግብ ማከፋፈያ ሊከፈቱ ይችላሉ።
   - መጀመሪያ ምግብ የሚቀርበው ዝግ በሆነ 3ኛው ቀን ላይ ይሆናል።

አስፈላጊ፡- የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ስርጭት ጣቢያዎች ክፍት የሚሆኑት በትምህርት ቤቱ ለተመዘገቡ ተማሪዎች ብቻ ይሆናል፣ እና የምግብ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ለሁሉም ተማሪዎች ክፍት አይሆኑም (ምንም አይነት ቨርቹዋል ማስተማር በማይኖርበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሲዘጋ እንደነበረው ማለት ነው)። ክፍያ እንዲቀርላቸው ማድረግ የሚቻለው በትምህርት ቤቱ ምግብ እንዲያገኙ ለተፈቀደላቸው ተማሪዎች ብቻ ይሆናል።

**988 የራስን ሕይወት የማጥፋት ሙከራ እና ቀውስ በሚፈጠርበት ጊዜ ክፍት የስልክ መስመር እና አጭር የጽሑፍ መልእክት ማስተላለፊያ መስመር**

ራሳቸውን ለማጥፋት ለሚሞክሩ ሰዎች ወይም በጭንቀት ውስጥ ላሉ ሰዎች 24/7 ነፃ እና ሚስጥራዊ የሆነ ስሜት የማረጋጋት ድጋፍ ይሰጣል። 988 ይደውሉ ወይም ቴክስት ይላኩ (24/7 ክፍት ነው)። TTY ተጠቃሚዎች የመልክት ማስተላለፍያ አገልግሎት መጠቀም ይችላሉ፤ ወይም 711 ቀጥሎ 988 መደወል ይችላሉ። አንላይን በእንግሊዝኛ ወይም በስፓንሽኛ ማነጋገር ይቻላል።



www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/virtual-instruction/